www.ginbot7.org

# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ሐምሌ 3 2000 ዓም ቁጥር 8

---

## ለሱዳን በተሰጠው መሬት የኢትዮጵያውያኑ ቁጣ እየነደደ ነው፡፡

## የሲያትልና ዋሽንግተን የጎንደር ተወላጆች ማህበር ቁጣውን ገለፀ፡፡

ከሑመራ እስከ ጋምቤላ ድረስ ያለውንና ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር፣ስፋቱ ደግሞ 50 ኪሎ ሜትር የሆነውን ለም መሬት የአቶ መለስ አገዛዝ በድብቅ ለሱዳን መንግስት በመስጠቱ በአገር ቤትም ሆነ በውጭው ዓለም በኢትዮጵያውያኑ ዘንድ የተቀሰቀሰው ቁጣ እያደር እየጋመ ነው።

በሲያትልና ዋሽንግተን የተቋቋመው የኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ይህንኑ አስመልክቶ ረቡእ ሰኔ 25 2000 አ.ም በርካታ ምሁራን የተሳተፉበት ስብሰባ ዋሽንግተን ላይ ከማድረጉም በላይ፤ በማግስቱ ሀሙስ ሰኔ 26 በወያኔ ኢህአዴግ ኤምባሲ ፊት ለፊትም በርካታ ኢትዮጵያውያን የተሳተፉበት የተቃውሞ ሰልፍ አስተባብሯል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሲያትልና ዋሽንግተን የጎንደር መረዳጃ ማህበር አባላት  በጉዳዩ ዙሪያ ሰሞኑን ያካሄዱትን ታላቅ ስብሰባ ሲያጠናቅቁ ባወጡት ባለ አምስት ነጥብ የአቋም መግለጫ፤ የአቶ መለስ አገዛዝ የፈፀመውን አገራዊ ክህደት አጥብቀው ከማውገዛቸውም ባሻገር ዳር ድንበራቸውን ለማስከበር የህይወት መስዋዕትነትም ቢሆን ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

“በታሪክ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን ይህን ታላቅ ጥፋትና ክህደት አጥብቀን እንቃወማለን፣በቁጭት ብቻም አናልፈውም”ያሉት ኢትዮጵያውያኑ፣ፍፁም ኢትዮጵያዊ ደምና ባህርይ የለውም ያሉትን የመለስ ን አገዛዝ እስከመጨረሻው እንደሚፋረዱት አስታውቀዋል።

በተመሳሳይ በተለያዩ የአውሮፓ፣የአፍሪካና የእስያ አገራት በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቁጣው እየተቀጣጠለ ይገኛል።